# ንጥር ሃብታችን ይመለስልን

ዮሐንስ አብርሃም ( ሎዛን፤ ስዊዘርላንድ)

መቻቻል 4ኛ ዓመት ቁ.1 (ሐምሌ Jul.2002)

ኢትዮጵያ ሐገራችን የልዩ ልዩ ሕዝቦች ስብስብ ስለመሆኗ በተለይ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል የለየለት የፖሊቲካ አግጣጫ ከወሰደና እነዚሁ በባህል፤ በቋንቋ፤ በሃይማኖት፤ በጐሣና በታሪክ የተለያዩ ሕዝቦች በግዴታ ውዴታና በፖሊቲካ ሽርክና የተዋሃዱ ወይም አንድ የሆኑ ሆነው በመሃከላቸው ተፃራሪ ሣይሆን ሊታረቅ የሚችል ዓይነት ልዩነት ስለመኖሩና፤ ገዢው መደብ የጋራ ጠላታቸው ስለሆነ ሲቻል በሰላማዊ ካልሆነ በዓመፃ መገርሰስ እንደሚገባው በተደጋጋሚ በአፅንዖት ማውሳትና ህዝቡንም በዚሁ አግጣጫ ማታገል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እንደሆነ የሚካድ አይደለም። የተደራጀ የፖሊቲካ መድረክ ባልነበረበት ወቅት የተማሪው ትግል ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ከመቻሉም በላይ ትግሉን ከላብ አደሩና ከመላ ጭቁን ህዝብ ትግል ጋር ማስተሳሰሩ በታሪክ ሲታወስ ይኖራል። የተማሪውን ትግል ይመሩ የነበሩት ወጣቶችና ምሁራን ልክ እንደ ሐገራቸው ሕዝቦች የተለያየ የጐሣ፤ የመደብ፤ የኃይማኖትና ርዕዮት ጭምር መሠረት ወይም አመጣጥ ይኑራቸው እንጂ እነዚህ ልዩነቶች የጋራ ትግል እንዳያካሄዱ አላገዷቸውም። የጋራ ትግሉ መሠረታዊ ዓላማ ጨቋኙን ሥርዓት ከመገርሰስ አልፎ ሕዝባዊ መሠረት ያለውና በሕዝቦች እኩልነት ላይ የተገነባ ብሔራዊ አንድነት ለመፍጠር እንጂ ሕዝቡን የመበታተን ዓላማ አልነበረውም። ትናንት ሣይወድ በግድ የተባበረ ሕዝብ ዛሬ ልዩነቱ ታውቆለትና ተከብሮለት በእኩልነት ላይ የተገነባ ሁነኛና አስተማማኝ አንድነት መፍጠር እንደሚቻልና ይኸው አንድነት መደባዊ እንጂ በጐሣ መስመር ላይ እንደማይሆን ጭምር ይፋ ያደረገ ትግል ነበር።

ዛሬ እነዚህ ሕዝቦች ለወያኔ ሥልጣን ሲባል በጐሣ ተዋቅረው ይገኛሉ። ኤርትራ ነፃ ወጥታለች፤ ይህንን ፈለግ በመከተል ሌሎች ነፃ ለመውጣት እየታገሉ ስለመሆናቸው ቢያንስ በየመፅሄቱና ጋዜጣ ላይ ይነበባል። የሕዝቡ ፍላጐት እስከሆነ ድረስ አንዳችም ኃይል ሊገታው የማይችል ናዳ ይሆናል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ትናንት ለነበረው ገዢ እነዚህ ሕዝቦች ሲገብሩ፤ ቀረጥ ሲከፍሉና በልማት ስም መዋጮ እየተባለ አፍንጫቸው ተሰንጐ ከየትም ብለው ጥቂቶችን በአንጡራ ሃብታቸው ሲያናጥጡ ኖረዋል። ቀረጥ ግለሰቦችን ማድለቢያ ሣይሆን የኤኮኖሚና ማህበራዊ አውታሮችን መዘርጊያ እንደሆነ፤ ቀረጥና ግብር ብሔራዊ ግዴታም ሆነ መብት ስለመሆኑ ሕዝባችን በውል ያላወቀበት ዘመን ነበር። መንግሥት ትምህርት ቤቶችን ለመክፈት፤ ሃኪም ቤቶችን ለማቋቋም፤ መንገዶችንና ድልድዮችን ለማሰራት፤ ማህበራዊና ባሕላዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋሞችን ለመገንባትና የሐገሪቱን ብሔራዊ ድንበርና የውስጥ ደህንነት ለማረጋገጥ የሚገለገልበት ወይም ሊገለገልበት የሚችለው ከሕጋዊ ግብርና ቀረጥ በተገኘ ገንዘብ እንጂ ፖሊቲከኞች ከኪሳቸው በሚያወጡት ገንዘብ እንዳልሆነ ተራው ሕዝብ በውል የማይረዳበት ጊዜ ነበር።

የአፄው መንግስት ለሕዝቡ ቀርቶ ለሰየመው እግዚአብሔርም ተጠያቂ አልነበረም። የግብርና ቀረጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ይገባል። ይህንንም ቢሆን ሕዝቡ በወሬ መልክ ይሰማ እንደሆነ እንጂ በውል የሚያውቀው ጉዳይ አልነበረም። እንደሚታወቀው ሁሉ ኢትዮጵያ የወርቅ ማዕድኖች አሏት። «ወርቅ የሚገባው ለነገሥታት እንጂ ለተራው ሕዝብ አይደለም» የሚል ፈሊጥ ነበር። ስለሆነም የሲዳሞና የወለጋ ወርቅ ምን ያህል ተቆፈረ፤ ምን ያህሉስ ተነጥሮ ለመጨረሻ ፍጆታ ዋለ ብሎ መጠየቅ የሚደፍር ማንም አልነበረም። ኃይለ ሥላሴ ሹማምንታቸውንና የንጉሣዊው አገዛዝ ወኪሎችን ይደልሉ የነበረው

ካጠራቀሙት መጠነ ሰፊ ወርቅ ትንሽ ቀረፍረፍ በማድረግ እንደነበር በዘመኑ የአደባባይ ምሥጢር ነበር። ኋላ የተካቸው አጅሬ ደግሞ የኢሠፓንና ቀደም ብሎም የአሠፓአኮን አባላት ደም ሥሩን ገትሮ ያወግዛት የነበረን ዩ.ኤስ አሜሪካን ዶላር እየቀነጫጨበ እንደነበር ቢያንስ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ «ቀይ እንባ» በሚል ርዕስ ከፃፉት መፅሃፍ ላይ የራሣቸውን ልምድ በመጥቀስ ካቀረቡት ሀተታ መረዳት ይቻላል።

ኃይለ ሥላሴ ከሚጠሩባቸ ዝናዎች አንዱ የምኒልክን ፈለግ ተከትለው ኢትዮጵያን ለዘመናዊ ሥልጣኔ ሊያበቋት ችለዋል የሚባለው ወሬ ነው። ነገርዬው ትንሽ እውነትነት ያለው ወሬ ነው። በዚህም አድራጐታቸው ይመሰገኑ ነበር። በእርግጥ አያሌ ትምህርት ቤቶችን፣ የክፈለ ሐገር ከተሞችን የሚያገናኙ መንገዶችን፣ ጥቂት ሐኪም ቤቶችን፣ በውጪ ካፒታሊስቶች የተቋቋሙ በጣት የሚቆጠሩ ፋብሪካዎችን፣ ባንኮችንና የኢንሹራንስ ኩባኒያዎችን በዘመናቸው እንዲገነባ አድርገዋል። ይህ ሁሉ ከኤክስፐርቲስ ሌላ የገንዘብ ወጪን ይጠይቃል። ኃይለ ሥላሰ ሲያርሱ፣ ሲነግዱ፣ ሲቆፍሩ ወይም ይህ ገንዘብ የተገኘበትን ሥራ በምንም ዓይነት ሁናቴ እንዳልሰሩ ግልጥ ነው። ያልለፉበትን ሃብት ነው ያካበቱት። በአምራቹ ሕዝብ ልፋትና ድካም የተገኘ ነበር የርሳቸው ሃብት። ደሞዝተኛ አልነበሩም። ገበሬ ወይም ነጋዴ አልነበሩም። መጠኑን ይህ ነው ብሎ በውል መናገር የማይቻል ግዙፍ ሃብት አጠራቅመው ነበር። እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ዓቢይ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ የሚሆነው። የዚህ ግዙፍ ሃብት ምንጭ ማን ወይም ምን እንደሆነ። ማን ነው የፈጠረው? እንዴትስ ሊፈጠር ቻለ? ብሎ መጠየቅ አግባብ ያለው ጥያቄ ነው። መብቱ ስለሆነ ሕዝቡ መጠየቅ አለበት። መብታችን ስልሆነ እኛም ልጆቹ መጠየቅ እንችላለን። ምናልባት ለምን አሁን ይነሣል ይህ ጥያቄ ማለት ይቻል ይሆናል። ይህም ቢሆን አግባብ ነው። እስከአሁን ይፋና ሕዝባዊ ጥያቄ ሆኖ ባለመነሳቱና ተገቢው ትኩረት ስላልተሰጠው ነው አሁን ይህ ጥያቄ ሊነሳ የቻለው። መገናኛ ዘዴዎችም ቀደም ባለው ዘመን እንደነበሩ ውሱን ባለመሆናቸውና በዓለማችን አራቱ አፅናፋት ተበታትነው የሚገኙ ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን በቀላሉ ሊገኛኙና ብሔራዊና ሕዝባዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ይፋ ውይይት ማካሄድ የሚቻልባቸው ዓለም አቀፍ መድረኮች የተፈጠሩበት ዘመን ነው። ባለፈው ትውልድ የደህንነት ሰዎችን ጭካኔ ፈርቶ ጨለማ ለብሶ የፕሮፓጋንዳ ሥራዎችን በስቴንሲል ቀርፆ በካርቦን ወረቀት አባዝቶ የሚሰራጭበት ዘመን አይደለም። በአጭሩ የተመቻቹ አውታሮች ስለተዘረጉ እነዚህን አውታሮች ከተራ ሰላምታና የግል ፎቶ ከመላላክ ይልቅ ለብሐራዊ ቁምነገር የምንገለገልበት ዘመን ስለሆነ አጋጣሚውን በመጠቀም ጐሣና ጐጥ በማይመለከታቸው የጋራ ጉዳዮች ላይ መወያየት ስለምንችል ነው። የብሔራዊና የሐገር ስሜት ቀርቶ አስተሳሰባችን ሁሉ በየጐሣችን አግጣጫ እየተጓዘ በመሆኑና ማንም ሊፍቃቸው የማይችሉ የተፈጥሮ ልዩነቶች ቢኖሩንም ሊያቀራርቡንና ሊያስተባብሩን የሚችሉ አያሌ የጋራ ጉዳዮች በመኖራቸውና ከነዚህም መሃከል አባቶቻችንና አባቶቻቸው ግፍ እየተፈፁመባቸው ከገዛ መሬታቸው እየተፈናቀሉ በለም መሬታቸው ሰፊና የንግድ ዘመናዊ እርሻዎች እየተቋቋሙ በንጉሣዊው ሥርዓት ቁንጮዎች ተከፋፍሎ ጥቂቶችን ሲያናጥጥ የነበረው፣ ወደ ውጪ እየወጣ የአንዳንድ የምዕራብ ሐገሮች ባንኮች ውስጥ ሲወሸቅ የነበረው ሃብት የሁላችንም በመሆኑ ትግሬ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ሲዳማ ሣይል ወይም ሰሜንና ደቡብ ብሎ ሣይለይ ከዘመነ ምንሊክ ጀምሮ ሲበዘበዝ የነበረ ሃብት የጋራችን ስለሆነ በሚለዩን የተፈጥሮ መስፈርቶች ላይ ማተኮሩ የከፋፍለህ ግዛን መሰሪ ዘዴ ለሚጠቀሙት ዕቡያን መሣሪያ እያደረገን ነውና ይህንን እውነታ ተረድተን በጋራና በአንድነት ከምናቀርባቸው ጥያቄዎች ውስጥ ይህ በውጪ ሀገር የተደበቀው ወርቃችን ባለቤት አልባ ሣይሆን የኛ ስለሆነ ይመለስልን ብለን ድምፃችንን ማሰማት አለብን ከሚለው ተነስተን ነው ይህንን ጥሪ ለማቅረብ የተነሣሣነው። በአጭሩ የቤታችንን አጥር ማጠር

ያለብን እኛ እንጂ ሌሎች ባለመሆናቸው ነው።

በዘጠናዎቹ አጋማሽ ውስጥ አንድ እንግሊዝ ሐገር የሚኖር ጃሜይካዊ ተወላጅ የአፄ ቴዎድሮስ ዘውድ ወደመጣበት መመለስ ይገባዋል በማለት የአያሌ የዜና አውታሮችን ትኩረት መሳብ መቻሉ አይዘነጋም። ይህ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ አይደለም። ስለኢትዮጵያ ሊቆረቆር የቻለው «ራስታ» በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም በአፍሪቃዊነቱም ተሰምቶት ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ ጥያቄው አግባብ ያለው ስለመሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። ለምን ቢባል፣ ዛሬ ሐገራችን እንደ ቅርጫ ሥጋ ተከፋፍላ ለበለጠ መበታተን ሥጋት የተጋለጠች ቢሆንም፣ ኢትዮጵያዊነት በኢትዮጵያ ድንበር የተወሰነ ጠባብ ክስተት ሣይሆን ለመላ ጥቁር ሕዝብ የነፃነትና አርነት አርማ መሆኑን ኢትዮጵያን ልናጠፋት ልንበታትናትና ልንበቀል ተዘጋጅተናል ለሚሉት ጠባቦች የዚህ ጃሜይካዊ ሥራ አርነት ሊሆናቸው ይገባል። ኢዮጵያዊነት ከትናንቱም ሆነ የዛሬ ገዢዎች አምሣያ ነፃ መሆን አለበት። ገዢ ባለበት ጭቆና አለ። ግፍ አለ። አንዱ የበላይ ሌላው የበታች ሆኖ ይታያል። ይህ እውነታ የሚያሳፍረን መሆን የለበትም። እኛ አልፈጠርነውምና። ሊያሳፍረን የሚችለው ግን ማንሣት የሚገባንን የጋራ ጥያቄዎች በቸልታ ወይም በፍፁም ደንታቢስነት ስናልፍ ብቻ ነው። የተከፈተን የጋራ በር ሣንዘጋ ስንቀር ነው።

አፄ ኃይለ ሥላሴ የተሰየሙት በእግዚአብሔር፣ ደርግ የተሰየመው በታሪክ፣ ወያኔ የተጠመቀው ደግሞ በጐሣ ጠበል ሆኖ ገዢዎች ምን ጊዜም ቢሆን የሥልጣን ጊዜያቸውን ለማራዘምና ዙፋናቸውን ለማጠናከር የማያደርጉት ነገር የማይሰሩት ቅጥፈት ሊኖር ስለማይችል ሕዝቡን ለማጃጃል ወደ ኋላ እንደማይሉ መታወቅ አለበት። ይህ አሁን የምናቀርበው ጥያቄ ሁል ጊዜ ልታጃጅሉን አትችሉም፣ ገበናችሁን ገልጠን አይተነዋል፣ ማንነታችሁን አውቀናል፣ የተፈጥሮ ልዩነቶቻችንን የጭቆና መሣሪያ ልታደርጉብን አትችሉም በማለት የጋራ ጉዳይ ላይ በጋራ ልንነሣ እንደምንችል ለገዢው ወገን የሕብረት ድምፅ መለከት ማሰማታችንም ነው።

ይህ ከሆነ ዘንድ ለምሣሌ አንድ ኤርትራዊ ማለትም የነፃዪቱ ኤርትራ ዜጋ በአያት ቅድመ አያቴ ዘመን የተዘረፈ ሃብት በእጅህ ላይ ይገኛልና ያንተ ስላልሆነ ለሕጋዊ ባለቤቱ ይመለስለት ብሎ አንድን የምዕራብ መንግስት ከመጠየቅ ምን የሚያግደው ነገር ይኖራል?

ጥያቄው ተራና ቀላል አይደለም። ሞራላዊ ብቻ ሣይሆን ሕጋዊም ነው። ታሪካዊም ጭምር በመሆኑ አግባብ ያለው ጥያቄ ነው። ይሁንና በአንድ እጅ ማጨብጨብ እንዳይሆን ቀደም ብሎ በኢትዮጵያዊነት ይጠሩና ይታወቁ የነበሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ እጆች ለዚህ ቅዱስና ሰላማዊ ጥያቄ አብረውና ተባብረው መነሣት፣ ትናንት አባቶቻችን የተገፈፉት ሃብት ብቻ ሣይሆን ክብራቸውን ጭምር በታሪክ ማህደር እንደገና መልሶ ማኖር ይሆናል። እነዚህ እጆች ከፍ ብሎ አጠር ባለ መልክ የተመለከቱ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ናቸው።

ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ዘመን ሕዝቦቿ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲመዘበር እንደነበረ መካድ አይቻልም። ከዚህ አንፃር ንጥር ሀብታችን ይመለስልን የሚለው የኢትዮጵያውያትና የኢትዮጵያውያን ጥያቄ አይመለከታቸውም የሚል ሰው ካለ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ነው ማለት ያዳግታል። ጥንት የሕዝቦቻችን ሃብት ካለአግባብ ሲዘረፍና በአውሮጳ ባንኮች ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ሲጠራቀም ስለነበረ ዛሬ ይህንን ዓቢይ ጥያቄ በጋራ የማናነሣበት ምክንያት የሚኖር ከቶም አይመስለኝም። በዚህ ረገድ ሰላማዊው ጥያቄያችን መልስ እንዲያገኝ በጋራ መረባረብ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል። ይህ ብቻም አይደለም ዛሬ በኛም ሆነ ነገ በኛ ልጆች መነሣት የሚገባቸው ገና ቋጠሮ ያላገኙ አያሌ የጋራ ጥያቄዎች በእንጥልጥል የቀሩ አሉ። ወርቃችን ይመለስልን የሚለው ጥያቄ ለነዚህ

የጋራ ጥያቄዎች አብረን የምናደርገውን ረዥም ጉዞ ከሚለኩት ዓይነተኛ መመዘኛዎች አንዱ ይመስለኛል።

ከላይ የቀረበው ጥሪ እንዲያውም ኢትዮጵያውያትንና ኢትዮጵያውያንን ብቻ አይመለከትም። ለፍትህና ለእውነት የቆመ ማንኛውንም ግለሰብ ወይም ሕዝብ ጭምር ይመለከታል። ፆታን፣ ርዕዮትን፣ ዜግነትን፣ ኃይማኖትን፣ ድንበርንና ዘርን ሣይለይ መቅረብ ያለበት ጥሪ ነው። ይሁንና ጥሪው በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ይፋ ከመሁኑ በፊት ባሉት መድረኮች መላ ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን በያሉበት መነጋገርና መወያየት ይጠበቅባቸዋል። ሣይመክሩበትና ተገቢውን ውይይት ሣያደርጉ በስሜታዊነት የሚጋለብበት ጉዳይ አይደለም። ሆ! ብሎ መነሣትና አካኪ ዘራፍ የሚሰኝበትም አይደለም። በመጀመሪያ ጥያቄው መነሣት በመርህ ደረጃ ተቀባይነትና ተገቢውን ትኩረት ማግኘት እንዳለበት ስምምነት ላይ መደረስ አለበት።

የምንከተለው ዘዴ ፍፁም ሰላማዊ ስለመሆኑ ጭምር ከወዲሁ መገንዘብ ያሻል። ስለዚህ ነጥብ ዝቅ ብሎ ተገቢው ትንታኔ ይቀርባል። ከዚያ አስቀድሞ ግን ከላይ የተጠቀሰው ጃሜይካዊ ስለ ቴዎድሮስ ዘውድ ምን አገባውና የይመለስ ጥያቄ ሊያቀርብ ቻለ የሚለውን ነጥብ በታሪክ ኮንቴክስት ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

ኢትዮጵያዊነት በኢትዮጵያ የፖሊቲካ ድንበር ብቻ የተወሰነ ክስተት ስላለመሆኑ ከዚህ በፊት በዚሁ መጽሔት ላይ በተለያዩ ጊዜያት አንስቼ እንደነበር የመቻቻል አንባቢያን አይስቱትም። ብዙ ጥንታዊ የታሪክ ምንጮች ኢትዮጵያን ከጥቁር አፍሪቃ ጋር አንድ አድርገው ያነሳሉ። ኢትዮጵያዊነት አፍሪቃዊነትም ጥቁርነትም እንደሆነ በውል ያመለክታሉ። እንዲያውም አንዳንድ ምንጮች ኢትዮጵያን ለጠፋው የአትላንቲስ ሥልጣኔ ምንጭነት ከታጩት ሐገሮች ውስጥ ይመድቧታል። በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ በኦሪቱም ሆነ አዲስ ኪዳን ተደጋግሞ ስሟ ይነሳል። በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ የአውሮጳ ካፒታል ጥሬ ሃብት በሚዳስስበት ወቅት የዘመኑ ሃያላን ሐገሮች አፍሪቃን እንደ ቅርጫ ሥጋ ሲከፋፈሏት በቅኝ ግዛት መስፋፋት አጥብቆ ያምን የነበረውና የሶስትዮሽ ህብረት አባል ክሪስፒ ወደ ኢትዮጵያ የላካቸው የአጣሊያ ወራሪ ሃይሎች በመላ ኢትዮጵያውያን ህብረት አድዋ ላይ የውርደት ካባ መከናነባቸ በዘመኑ ታላቅ ዜና ነበር። እንዴት አንድ አፍሪቃዊ ሐገር የአውሮጳን ሃያል መንግስት ሠራዊት ሊያቸንፍ ይችላል የሚል ነገር የአጣሊያን የውስጥ እግር ሲለበልብ ለመሳዎቿ ግራ የሚያጋባ ሆኖ ለጥቁር ዘር ግን መታፈሪያቸው ነበር። ይህ ሁሉ ተደማምሮ ከአፍሪቃ በባሪያነት ተሸጠው በተለይ በአሜሪካ ሁለቱም ክፍለ ዓለሞች ተሰራጭተው ለነበሩ ጥቁሮች የዘር ግንዳቸው የተከበረ መሆኑን የሚያሳይ ታሪካዊ ሁነት በማንነታቸውና ምንነታቸው እንዲኮሩ አደረገ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ነው ለምሣሌ ጃሜይካውያን ያሉበትን ሐገር እንደባቢሎን ኢትዮጵያን ደግሞ እንደ ፅዮን አድርገው እንዲተረጉሙ ያበቃቸው። ተምሣሌትነቱ ባቢሎን የጥንት እስራኤላውያን በባርነት ታግተው ለዘመናት የቆዩበትንና ወደ ኢዬሩሳሌም ማለትም ወደ ፅዮን ለመመለስና ነፃነታቸውን እንደገና ለመቀዳጀት ይመኙ በነበረው እምነት ላይ የተመሠረተ ነው።

ከፍ ብሎ በምሣሌነት ያነሳሁት ጃሜይካዊ አንድ ምሣሌ ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ ብዙ ጃሜይካውያን ወደ እናት ሐገራችን ኢትዮጵያ እንመለስ በማለት ከፍተኛ ዝግጅት ያደርጉ እንደነበረ ይታወቃል። በራስታዎች እምነት ኃይለ ሥላሴ ነቢይም አምላክም ናቸው። እስከአሁንም በሕይወት እንዳሉ ያምናሉ። ከዚህ ሃይማኖታዊ እምነት በመነጨ ሁናቴ ነው ይህ ወጣት ጃሜይካዊ የቴዎድሮስ ዘውድ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ

አለበት ብሎ የእንግሊዝን ዘውድ የሞገተው። ኢትዮጵያዊነት በኢትዮጵያ የፖሊቲካ ድንበር የተወሰነ አይደለም ማለት የሚቻልበትም አንዱ ምክንያትም ለዚህ ነው። በእርግጥ እንነጋገር ከተባለ ኢትዮጵያ ያጣቻቸው አያሌ ዕፁብ ድንቅ የታሪክ ቅርሶች ከሐገር ውጪ ይገኛሉ። ባለማወቅም በመታለልም ሆነ በደረሰባት ተደጋጋሚ የውጪ ወረራዎች መንስዔ ባህላዊ፤ መንፈሳዊና ታሪካዊ ቅርሶች ተዘርፋለች።

ከነዚህ ቅርሶች ሌላ ሆዳምና ሌባ መሪዎቿ ለሐገር ልማትና እድገት ማሰብን ወደ ጐን አድርገው በሥልጣን ኮርቻ ላይ በተፈናጠጡ ቁጥር የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለፍተውና ደክመው ያፈሩት ንዋር ሃብታቸው የባዕዳንን ቱጃሮች እንዲያናጥጥና የኢትዮጵያ ልጆች ምፅዋተኛ እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል። የዚህ ፅሁፍ መሠረታዊ ዓላማም ይህንን ካለ አግባብ የተዘረፍነውን ሃብት ለባለመብቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመለስበትን ሁናቴ መላ ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን ባገኙት መድረክ ሁሉ በያሉበት እንዲመክሩበት፤ እንዲወያዩበትና ተገቢውን ትልም እንዲያበጁ ለመማጠን ነው።

መናገር ቀላል ነው። የተናገሩትን በተግባር መተርጐም ግን ያስቸግራል። በመጀመሪያ ደረጃ በጉዳዩ ላይ ማመን ያስፈልጋል። ይህም ማለት የይመለስ ጥያቄው ተገቢ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመርህ ላይ የተመሠረተ እምነት መኖር አለበት። መሠረታዊ መርሁ ብሔራዊና የሕዝብ ክብር ጉዳይ ነው። ከዚሁ የተያያዘ ሌላው ጉዳይ የመብት ጥያቄ ነው። በብሔራዊና ሕዝባዊ ክብር እምነት የሌለው ትውልድ ለመብቱ ማለትም ለግል መብት ይጋፈጣል ብዬ አላምንም። በኢኳያውም አንድ ሰው እራሱን የማያከብር እስከሆነ ድረስ ለሌላው ክብር ሊጨነቅ ቀርቶ ሰብአዊ ክብር ምን እንደሆነ እንኳ የሚረዳ አይመስለኝም። ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ያለንን ክብር የምንገልጥበት አንዱና ዓይነተኛው መንገድ መብታቸውን ማክበርና ማስከበር ነው። በዚህ መሠረታዊ መርህ እምነት እስከሌለን ድረስ ካለአግባብ የተመዘበረችው ሐገራችንና ከአብራኩ ያወጣን ሕዝቧ መሃን እንደሆኑ ሊቆጠር ይገባል። በመሠረታዊ መርሁ እምነት እስካለንና በራሳችን የምንተማመን ከሆነ የፈጀውን ጊዜ ይፍጅ እንጂ የምንናገረውን በተግባር የማንተረጉምበት ወይም የማናስተረጉምበት አንዳችም ምክንያት ከቶውንም አይኖርም።

ይህ ከሆነ ዘንድ ምን ዓይነት ዘዴ መጠቀም አለብን፤ የት፤ እንዴት፤ በየትኛው መድረክ፤ በማንስ መሪነት ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። ለነዚህና ለመሳሰሉ ጥያቄዎች ጠቅለል ባለ መልኩ አግጣጫ ሊጠቁሙ የሚችሉ መሪ ሃሳቦችን በንድፍ መልክ ማቅረብ ይቻላል። ንድፉ እንደ ስዊስ ፎርማጆ እዚያም እዚህም ቀዳዳ ሊኖረው ይችላል። ይህንን ክፍተት ማሟላት የማን ኃላፊነት እንደሆነ መናገሩ አያሻም።

ሐገራችን በሚያሣዝንና በሚያሣፍር ሁናቴ ድሃ ናት። ግን ይህንን ዓይነት ድህነት እኛ ስላልፈጠርን ልናፍርበት አይገባም። አንድ ሰው ባልሠራው ነውር ተግባር ማፈር አይችልም፤ የለበትምም። ማፈር የሚገባቸው ከሕዝቡ አፍ እየተነጠቀ በተካበተው ሃብት የናጠጡ ወይም የነዚህኑ ፈለግ ተከትለው ለሕዝቡ ደንታ የሌላቸው ወገኖች ናቸው። እንደ አይሁዳኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዋቀረ ሎቢ የለንም። ኢትዮጵያ እጆቿን መዘርጋት የምትችለው ወደ ገዛ ልጆቿ ብቻ ነው። ብዙ አጋርና ወዳጅ የላትም። የትግራይ፤ የወሎ፤ የሸዋ፤ የሐረርጌና የባሌ ሕዝብ በረሃብ እንደ ቅጠል በሚረግፍበት ጊዜ የኢትዮጵያ ገዢዎች በሻምፓኝና በውስኪ ይራጩ ነበር። ተመልካቹ ሁሉ እንባውን የተራጨበትን የጆናታን ዲምቢልቢይ ፊልምና የአንጋፋው የዘፈን አርቲስት ያንቀረቀረው የዋይታ ዘፈን የቅርብ ጊዜ ታሪካዊ መዘክር ናቸው። ታሪክ ብዙም ሣይቆይ ተደገመና ደርግ እንግልቱውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአዋጅና በድርጅት በሚያሳክርበትና በፍርሃት ሃይል ይገዛ በነበረበት

ዘመን ዳግመኛ ትራዠዲ ደረሰብን። ሐገርና ሕዝብ በውል ተረስተው የሐገሪቱ መዲናና ዋና ከተሞች ጨርቅና መፈክር ተላበሱ። ዓመታዊ ስታቲስቲክስ ዕድገት ሲያወራ እውነታው ሌላ ሆኖ ተገኘ። ከተፈጥሮ ጭካኔ ይልቅ ሰው ሰራሽ ጭካኔ ሕዝቡን ለረሃብና ችጋር ዳረገው። ከዚህ ዓይነት ሰቆቃ አሁንም አልወጣንም። የሕዝቡ አንጡራ ሃብት በድልድይ፣ ሀኪም ቤት፣ የውሃ መስኖ፣ መንገድ፣ የተሻሉ ትምህርት ቤቶች ወዘተ ግንባታ ላይ መዋል ሲገባው ከፊሉ ከሐገር እየወጣ የምዕራብ ሐገሮችን ባንኮች ማድለቢያ ሆነ። የተዛባ የፖሊቲካ ሠርዓት የተዛባ የኤኮኖሚ ሥርዓትን ወለደ። ስለ ኢትዮጵያ ልማትና ዕድገት የሚጨነቁትና ኤኮኖሚው በአዲስ መንገድ መዋቀር አለበት የሚሉት ሌሎች ሆኑ። ሀያኛው ክፍለ ዘመን ያልጨረሰውን የብዝበዛ ሥርዓት ሀያ አንደኛ ክፍለ ዘመን ዓለማችን አንዲት መንደር ሆናለች በማለት እየኮረኮረን ግሎባላይዜሽን በሚሉት መልኩና ስሙ ገና በውል የማይታወቅ ጭራቅ አሣሣች መጐናፀፊያ ሽፋን በሥውርም በይፋም የብዝበዛ አውታሩን ዘረጋብን። ይህ በእንዲህ እንዳለ ቀደም ባሉት ዘመናት ከሐገር ወጥቶ የነበረው ሃብታችን ጉዳይ ቄሱም ዝም መፅሃፉም ዝም ሆነ። ስለሆነም አሁን የይመለስልንወርቃችን ጥያቄ ከመቸውም የበለጠ የምንነጋገርበት ርዕስ መሆን ይገባዋል።

የምንከተለው ዘዴ ሰላማዊ ነው። ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መረታዊ መርህ እስከ አመንን ድረስ ይበልጡን ደግሞ በራሣችንም ይሁን በምንሰራው ሠራ ፅኑ እምነት እስካለን ድረስ በጉዳዩ ላይ ይፋ ውይይት መክፈት ይቻላል። በጋዜጣ፣ በመፅሄት፣ በኢንተርኔትና በመሳሰሉ መድረኮች ላይ ሣንፈራ ወይም ሣናፍር የሚሰማንን ይፋ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በኛው ውስጥ ጉዳዩ በሚገባ ተተችቶ ሥር እንዲሰድ ያሻል። በመቀጠልም በብሔራዊና ዓለም አቀፍ በሆኑ ድርጅቶች መድረክ ጥያቄያችን እንዲሰማ «ፐቲሽን» ማቅረብ ይቻላል። በተለይ ስለ ዓለምአቀፍ ግንኙነት እውቀቱና ልምዱ ያላቸው ግለሰቦችና የሕግ ጠበብት ሕጋዊና የሚያዋጡ አግጣጫዎችን በማሣየት ረገድ መሪ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ይገባልም። እነዚህ ጠቢባን የሚሰጡት ምክር ወይም ሃሳብ በጅምር ደረጃ እንኳ ወሳኝነት አለው። ምክንያቱም ማንም ግለሰብ ወይም ቡድን በማያዋጣው ጉዳይ ላይ ጊዜውንና ጉልበቱን ሊያባክን አይገባም። ይህ ሲባል ደግሞ ከወዲሁ የስንፍና ቦይ መቀደድና ግለኝነት ሰፍኖ ይህን የመሰለ ግዙፍ ብሔራዊና ሕዝባዊ ጥያቄ ገና በእንጭጩ እንዲቀጭ ቀዳዳ መክፈት አያስፈልግም። ወሣኙ የመረጃ ጥያቄ ሊሆን ይችላል። መቼና እንዴት በማን ወይም የት የሚሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ማግኘት አለባቸው። ለምሳሌ ደርግ ሥልጣኑን በሚያጠናክርበት ጊዜ የከርታታውን ሕዝብ እይታ በተራ ፕሮፓጋንዳና ቅጥፈት ለማጨናበስ ይህን ያህል ቢሊዮን ዶላር በስዊስ ባንኮች አፄው ያስቀመጡት እያለ እቴ እንዴት ትራቢያለሽ? ወንድም አንተስ ባዶ አንጀትህን እንዴት ታቅፈህ ታድራለህ? በማለት ያቀረበውን እንደ ሕጋዊ ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል ሆኖ ሊወሰድ አይችልም ይሆናል። ይሁንና ጪስ እሳት ባልነደደበት ስለማይወጣ ይህ የደርግ መረጃ ቢያንስ በመንደርደሪያነት ሊነሳ የሚችል ይመስለኛል። ሌሎች ምንጮች እንዳሉ ሆኖ።

ሆነም ቀረም ተዘርፈናል። ይህ መቼም ቢሆን አሌ የማይባል ሐቅ ነው። ፅዳቱ መጀመር የሚገባው ደግሞ ከቤት ነው። ከሐገር ሣይወጣ በሐገር ውስጥም የሕዝቡ ሃብት ካለአግባብ ተዘርፎ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ማንደላቀቂያ ሊሆን ይችላል። እግዜር ያሳያችሁ እስቲ የገዛ ወገኑ መጠጊያ መጠለያ አጥቶ በረንዳ አዳሪ በሚሆንበት ሐገር ገገርው ክፍል በምቾትና ቅንጦት መንደላቀቅ ተገቢ ነው? ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን በትምህርትና ሥራ ላይ ማዋል የሚገባቸው ወጣቶች ሥርዓቱ በጫነባቸው ግፍ የጐዳና ተዳዳሪ ሆነውስ እንዴት ይቀራሉ? የራሣቸውን ምቾትና የንደላቀቁበትን ሣንዘነጋ የገዛ ሕዝባቸውን መመገብ ያልቻሉ መሪዎች የመሪነት ስምና ክብር የሚገባቸው አይመስለኝም። እነዚህና መሰል

አያሌ ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል። ግን ጥረቱ ጥያቄ በመጠየቅ መወሰን የለበትም። ቃል ወደ ተግባር መለወጥ የግድ ነው። ሕዝባችን የተዘረፈውን ሃብት፣ የተገፈፈውን መብት፣ ያጣውን ክብርና ብሔራዊ ልዕልናውን መልሶ እንዲያገኝ መታገል የዚህ ትውልድ ግዴታም ሃላፊነትም ነው። ትግል ሌሎች መስፈርቶቹ እንደተጠበቁ ሆኖ ስልትን፣ ዘዴን፣ ድርጅትን፣ መርህንና ከሁሉም በላይ የዓላማ ፅኑነትን ይጠይቃል። ይህ ግዙፍ ሥራ በጥቂት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ብቻ የሚካሄድ ሊሆን አይችልም፣ አይገባውምም። ማንኛውም ትግል መሪ ያስፈልገዋል። መርሃ ግብሩ እውን የሚሆንበት መድረክ ያስፈልገዋል። የቀረበው ጥያቄ ጠባብ አይደለም። ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ሁሉ ጐሣን፣ ጐጥን፣ ሃይማኖትን፣ ርዕዮትን ያታን ወዘተ እንደመመዘኛ አይከተልም። ጥረቱ ብሔራዊም ዓለም አቀፋዊም ነው። የሚከተለው ዘዴ ደግሞ ፍፁም ሰላማዊ መሆን ይገባዋል።

ይህ ሰላማዊ ዘዴ በሕዝባዊ እምቢተኝነት መርህና መሣሪያነት ተመርኩዞ እንደ ተመድ ያሉትን ዓለም አቀፋዊና በይነ መንግስታት መድረኮችን በመገልገል ባለ ጉዳዩ የሆነውን ሕዝብ በማሣተፍ ድምፁን በአቤቱታ መልክ ማሰማት የሚቻልበት ትግል ይሆናል። እዚህ ላይ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ ለአንባቢያን መጠቆም ምናልባት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ሕዝባዊ እምቢተኝነት የሰላማዊ ትግል ዓይነተኛ መልክ ነው። መንግሥት ላይ በተለያዩ ዘዴዎች አማካይነት ተፅዕኖ ማድረግን ይጠቁማል። የተዛባን አስተዳደር ወይም ሕግ ለመለወጥ ተገቢውን ሕግ መጣስን ጭምር ያመለክታል። ፅኑ እምነትና ዓላማ ላለው ትግል ሕዝባዊ እምቢተኝነት የሚሰጠው ጥቅም ከትጥቅ ትግል ያነሰ አይደለም። ለሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላትና መሪዎች ፒቲሽን በማቅረብ፣ ሰላማዊ ሰልፎችን በማድረግ፣ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው ሀገሮች መንግስታትና መሪዎች ይፋ ደብዳቤዎችን በማቅረብ፣ የነዚህኑ ሐገሮች የዜና አውታሮች በጥያቄው ላይ እንዲወያዩና እንዲያወያዩ በመቀስቀስ፣ መንፈሣዊ መሪዎች በጉዳዩ ላይ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ በመጠየቅ፣ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን፣ የታወቁ ምሁራንን፣ እውቅና ዝነኛ የፊልም፣ የሙዚቃና ሌሎች አርቲስቶችን፣ የፕሬስና ሌላ የዜና አውታር ሰዎችን፣ ወጣቶችንና ሲቪክ ድርጅቶችን በማሣተፍ ከአይሁዳን ሎቢየበለጠ ሰፊና ሊናጋ የማይችል ዓለም አቀፍ ድጋፍ ማሰባሰብ ይቻላል። በኔ እምነት የመሪነቱን ሚና በግንባር ቀደምነት መጫወት ያለበት ወጣቱና በወጣቱ ዙሪያ የተዋቀሩ መድረኮች መሆን ይገባቸዋል። ይህ ሲባል የሕዝቡ ተሳትፎ ወሳኝነት እንደአለው መዘንጋት የለበትም። ባለመብቱ እርሱ ነውና። ይህንን ጥረት እስካላደረግንለት ድረስ ሕዝባችንንም ይሁን ሐገራችንን መሃን እናደርጋቸዋለን። ከዚህ ብሔራዊ ጉዳይ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ትልቅ ሽንፈት ነው። ሐገሬ ወይም ሕዝቤ ብለን አፍ ሞልተን ልንናገር የምንደፍረው በጉዳዩ ላይ አምነንበት የምንችለውን ስናደርግ ብቻ ነው።